# Symbicort® Turbuhaler®

80/4.5 160/4.5 320/9 μg/inhalation[1]

# ይክፈቱ ያዞሩ እና ወደ ውስጥ ይተንፍሱ

**Symbicort Turbuhaler** የተለያየ መጠን ያለው የአስም መድኃኒት መንፈያ ሲሆን በጣም አነስተኛ መጠን ያለው ደቃቅ መድሃኒት ይሰጣል።

በ Turbuhaler አማካይነት የአስም መድኃኒት ሲነፉ፣ ደቃቅ መድሃኒቱ ወደ ሳምባ ይተላለፋል። ስለሆነም፣ በጫፉ ላይ ባለዉ ክብ ቀዳዳ አማካይነት በደንብና በሃይል ወደ ውስጥ መተንፈስ ያስፈልጋል።



1 ክዳኑን ለመንቀል ያዙሩት። ክዳኑ ሲነቀል ‹ጠቅ› የሚል ድምፅ ያሰማል፡፡



2 የአስም መድኃኒት መንፈያውን ቀጥ አድርጎ በመያዝ ቀዩን መያዣ ወደታች ያድርጉት። መያዣውን በሚያዞሩበት ወቅት ጫፉ ላይ ያለዉን ክብ ቀዳዳ  ይዘው አይቆዩ። የአስም መድኃኒት መንፈያው ውስጥ የመድሃኒት መጠን ለመሙላት፣ መያዣውን እስከመጨረሻው ድረስ በአንድ አቅጣጫ በኩል በማዞር ከዚያም ወደተቃራኒ አቅጣጫ ይመልሱት። መጀመሪያ ላይ በየትኛዉም አቅጣጫ ቢያዞሩት ለዉጥ አያመጣም በዚህ ሒደት መጨረሻ ላይ፣ ጠቅ የሚል ድምጽ ይሰማል። (አዲስ የአስም መድኃኒት መንፈያን ለመጠቀም በሚያዘጋጁበት ወቅት፣ ሒደቱ ሁለት ጊዜ መፈጸም አለበት)። የአስም መድኃኒት መንፈያው አሁን መድሃኒት ሞልቶበታል ስለዚህ ለአገልግሎት ዝግጁ ነው።



3 ወደ ውጭ ይተንፍሱ።  ጫፉ ላይ ባለዉ ክብ ቀዳዳ በኩል ወደ ውጭ አይተንፍሱ።

4 ጫፉ ላይ ያለዉን ክብ ቀዳዳ በቀስታ በጥርስዎ መካከል ያስገቡት፣ ከንፈርዎን ገጥመው በደንብ በሃይል በአፍዎ ወደ ውስጥ ይተንፍሱ።

5 ከአንድ ጊዜ በላይ ወደዉስጥ እንዲስቡ በሃኪም ከታዘዘ ፣ ከ2 እስከ 4 ያሉትን ሂደቶች ይድገሙ።

6 ክዳኑን በደንብ ጠበቅ አድርገው በመክደን ወደቦታው ይመልሱ።

7 አፍዎን በውሃ ያለቅልቁ።  ውሃውን አይዋጡት።

**የአስም መድኃኒት መሳቢያ**

ጫፍ ላይ ያለዉን ክብ ቀዳዳ ዉጨኛዉን ክፍል በተከታታይ (በሳምንት አንድ ጊዜ) በደረቅ ሶፍት ያፅዱ

**ጫፍ ላይ ያለዉን ክብ ቀዳዳ ለማጽዳት ውሃ ወይም ሌሎች ፈሳሾችን አይጠቀሙ።**

## የአስም መድሃኒት መሳቢያ መሳሪያዉን መቀየር ያለብዎት መቼ ነዉ?







- የመድሃኒት መጠኑን መጠቆሚያ(ምስል ኤ) የአስም መድኃኒት መሳቢያዉ ውስጥ የቀረውን የዶዝ መጠን የሚያሳይ ሲሆን ከ ከ 60 ይጀምራል ወይም ሙሉ ሲሆን ከ 120 ይጀምራል
- የመድሃኒት መጠኑን መጠቆሚያ በ 10 የመድሃኒት መጠን ተከፋፍሎ የተቀመጠ ሲሆን እያንዳንዱን የመድሃኒት መጠን አደራረግ አያሳይም፡፡ በመድሃኒት መጠን መጠቆሚያ ውስጥ እንቅስቃሴ ባያዩም Turbuhaler የመድሃኒት መጠኑን እንደሚቆጣጠር እርግጠኛ መሆን ይችላሉ።
- በጠቋሚው መስኮት ጠርዝ ላይ ቀይ ምልክት ሲያዩ፣ ወደ 20 የሚጠጋ መድሃኒት ይቀራል ማለት ነው። ለመጨረሻዎቹ 10 የመድሃኒት መጠኖች የመድሃኒት መጠን ጠቋሚው የቀይ ምልክት በስተኋላ ያሳያል። የዜሮ ምልክቱ የመስኮቱ መካከል ላይ ሲደርስ (ምስል ቢ)፣ የአስም መድኃኒት መሳቢያዉን ያስወግዱ።



- እባክዎ ይህንን ይገንዘቡ፤ የመድሃኒት መጠን ጠቋሚዉ 0 ላይ ቢደርስ እንኳ፣ መያዣው አሁንም ሊዞር ይችላል ነገር ግን ጠቋሚው መንቀሳቀስ አቁሞ የዜሮ ምልክቱም መስኮቱ ላይ ይቀራል።
- የአስም መድኃኒት መሳቢያዉን ሲወዘውዙት የሚሰማው ድምጽ መንስኤው መድሃኒቱ ሳይሆን ማድረቂያው ነው። በመሆኑም፣ ድምጹ በ Turbuhaler ውስጥ የቀረውን የመድሃኒት መጠን አያመለክትም።
- ዶዙ ከመወሰዱ በፊት የመጫን ሂደቱን ከአንድ ጊዜ በላይ ካከናወኑ፣ የሚሰጥዎት የመድሃኒት መጠን አንድ ብቻ ነው። የመድሃኒት መጠን ጠቋሚው ሁሉንም የተጫኑ የመድሃኒት መጠኖች ይመዘግባል።
- መድሃኒቱ ቢያልቅም እንኳን ዘወር ቢያደርጉት "ጠቅ" የሚል ድምፅ ከአስም መድኃኒት መሳቢያዉ ይሰማሉ።

### ከመጠቀምዎ በፊት የተጠቃሚዎችን በራሪ ወረቀት ይመልከቱ

መረጃው እ.ኤ.አ ታህሳስ 2018 ጀምሮ ትክክለኛ ነው።
ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ፋርማሲስቱን ወይም ሃኪምዎን ይጠይቁ።

ማጣቀሻዎች፡
Symbicort® Turbuhaler® መድሃኒቱ የታዘዘበት መረጃ(80/4.5, 160/4.5, 320/9 mcg/inhalations) በ MOH ፈቃድ የተሠጠዉ

Side effects can be reported by clicking safety.Israel@astrazeneca.com

AstraZeneca

Symbicort®የAstraZeneca ድርጅቶች ግሩፕ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ነው። የ AstraZeneca አርማ የ AstraZeneca ድርጅቶች ግሩፕ የንግድ ምልክት ነው።

**AstraZeneca Israel.** 1 Atir Yeda Street., Building O-Tech-2 P.O.B. 8044
Kfar Saba, 4464301 Israel Tel: 09-7406528 Fax: 09-7406527

IL-1837 MAR 2021

# Symbicort®
**budesonide/formoterol**

# Turbuhaler
# የአጠቃቀም መመሪያ

אתר הדרכה:
Mysymbicort.co.il
סיסמא: לנשום

SCAN ME